የዋስትና ህግ መሠረታዊ ሃሳብ እና አፈፃፀሙ

ከፕሪዝን ፈሎውሺፕ ጋር በመተባበር ለክልሉ ዳኞች የተዘጋጀ ሥልጠና

አዘጋጅ፦ ፀጋዬ ወርቅአየሁ
የጠቅላይ ፍርድ ቤት
ዳኛ

ጥር 11-12 ቀን 2004 ዓ.ም

ባህር-ዳር

ማውጫ

- ጽንሰ ሃሳባዊ መሠረቱ
- የዋስትና መብት በኢትዮጵያ ህግ
    - መርህ
    - ልዩ ሁኔታ
- ስለሚቀርብበት ቦታ
- አዲስ ነገር
- በዋስትና አካባቢ የሚታዩ ችግሮች

ጽንሰሃሳባዊ መሠረቱ

- በአንድ በኩል ተጠርጣሪዎች የሚቀርብባቸውን ክስ መጋፈጣቸውን በማረጋገጥ እና በሌላ በኩል ደግሞ ከፍርድ በፊት ነፃ ሆኖ የመገመትን የግለሰብ መብት በማስጠበቅ መካከል ያለውን ሚዛን መጠበቂያ መሣሪያ ነው።

- በአንድ በኩል የግለሰቦች የግል ህይወት ባለማወክና በሌላ በኩል ሰዎችን አሥሮ በማቆየት በህብረተሰቡ ላይ የሚደርሰውን ወጪ እንዲሁም በዚህ የተነሳ የሚመጣውን ማኅበራዊ ጫና በመቀጣጠር መካከል ምርጫን በመውሰድ ሚዛን የምንጠብቅበት መሣሪያም ነው።

የዋስትና መብት በኢትዮጵያ ህግ

- መርህ
- የወ.መ.ሥ.ሥ.ህ. ቁ.63
- “... የሞት ቅጣትን ወይም አሥራ አምስት ዓመት ወይም በላይ የሆነ ጽኑ ዕሥራት የሚያስቀጣው ከሆነና ወንጀል የተፈፀመበት ሰው በደረሰበት ጉዳት የማይሞት የሆነ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ..... ለመልቀቅ ይችላል” ይላል።

- በብዙ ቦታዎች እስካሁን ድረስ ዋስትናን የሚከለክሉት አንድ ሰው ከአሥራ አምስት ዓመት በማያንስ ዕስራት ሊቀጣ የሚችል ሲሆንና በወንጀሉ ድርጊት ምክንያት ሰው የሞተ ወይም የሚሞት የሚመስል እንደሆነ ብቻ ነው።

- በሌላ በኩል ግን በተለየ አስተሳሰብ ነገሩን የሚረዱት ሰዎች ህጉን ዋስትና ከመፍቀድ አንፃር ነው የሚያዩት። ሃሳባቸው የሚነሳው ከዚህ ነው። ዋስትና የሚፈቅደው ይላሉ ግለሰቡ አሥራ አምስት ዓመትና ከዚያ በላይ የሚታሠር ካልሆነ እና የሞተ ሰው የሌለ እንደሆነ ነው። እና የሚለው ቃል ዋስትና ለመፍቀድ ዓላማ እንጂ ለመከልከል ከሁለት አንዱ መJላቱ ብቻ በቂ ነው ይሆናል ይላሉ። ለማስከልከል ዓላማ ከአሥራ አምስት ዓመት በላይ የሚያስቀጣ መሆኑ ብቻውን ይበቃል ማለታቸው ነው።

የሁለተኛውን ሃሳብ በሂሳባዊ ስሌት ማየት ቀላል ሳይሆን አይቀርም

- ህጉ የተቀረፀው ዋስትና ከመፍቀድ አንፃር ስለሆነ ስሌቱን በዚሁ አግባብ እንየው ፤ መርሁ
  - <15 ዓመት የሚያስቀጣ + ሞት ካሌለ = ዋስትና ይፈቀዳል፤ ከዚህ በ|ላ የሚያስከለክልበትን ሁኔታ እንተንትነው

- ≥ 15 ዓመት የሚያስቀጣ + ሞት ሳይኖር ≠ ዋስትና መፍቀድ (ዋስትና ይከለከላል ማለት ነው) ወይም
- < 15 ዓመት የሚያስቀጣ + ሞት ሲኖር ≠ ዋስትና መፍቀድ (ዋስትና ይከለከላል ማለት ነው)

- ስለሆነም ዋስትና ለማስከልከል ሁለት ሁኔታዎች ያስፈልጋሉ ማለት ነው። እነሱም
  - አሥራ አምስት ዓመት እና ከዚያ በላይ የሚያስቀጣ መሆን ወይም
  - የሞት መኖር
- ስለዚህ ጥምረት የሚያስፈልገው ለማስፈቀድ ብቻ ነው ማለት ነው።
- የትኛውን ሃሳብ ይደግፉ? ለምን ?

የዋስትና ልዩ ሁኔታ

- ልዩ ሁኔታ
- የወ.መ.ሥ.ሥ.ህ. ቁ. 67

- ዋስትና የሚከለከለው
  - “... ግዴታዎቹን..... የሚፈጽም የማይመስል...”
  - “... ሌላ ወንጀል ይፈጽም ይሆናል ተብሎ ሲገመት....”
  - “... ሌላ ወንጀል ይፈጽም ይሆናል ተብሎ ሲገመት....”
  - “... ምስክሮች የሚሆኑትን በመግዛት... አስረጂ የሚሆኑትን ያጠፋ ይሆናል ተብሎ የሚገመት ሲሆን... “ ነው።

- የሚፈጽም የማይመስል፣ ተብሎ ሲመት የሚሉት ን የሚመዝነው ፍርድ ቤት ነው።
- የሚመዝነው በተከራካሪው ዓቃቤ ህግ የሚቀርብለትን ፍሬ ነገር ነው።

- የመዛኙን ቀልብ ለመሳብ ተጨባጭ የሆኑ መነሻዎችን ማቅረብ ይጠይቃል። በሁለት ምክንያት
  - ልዩ ሁኔታ እንደመሆኑ መጠን በጠባቡ መታየት ስላለበት
  - ግምቱ ቀላልና ልቅ ከሆነ መለኪያውን መርህ የማድረግ ውጤት ስለሚኖረው

አዲስ ነገር [የወ.መ.ሥ.ሥ.ህ.ቁ. 74]

- አንድ ጊዜ በተወሰነው በዚያው ነጥብ ላይ ነገሩን መልሶ ማየት አይገባም በሚል መሠረት ላይ የቆመ ሃሳብ ነው።
- አዲስ ነገር መኖር አለበት
  - በጊዜው ያልነበረ ወይም
  - በጊዜው የነበረም ቢሆን ግን ያልታወቀ ማለት ነው
- አዲሱ ነገር
  - ከፍርድ ቤቱ መረዳት ወይም
  - በማናቸውም ባለጉዳይ አማካኝነት ሊቀርብ ይችላል። ለምሳሌ
    - የዋሱ መሞት
    - ሊጠፋ በዝግጅት ላይ መሆኑን መረዳት ወዘተ...

የዋስትና አቤቱታ ስለሚቀርብበት ቦታ [የወ.መ.ሥ.ሥ.ህ.ቁ. 64(3)]

- በማናቸውም ፍርድ ቤት ነው።
- ማናቸውም ማለት
  - ማናቸውም መደበኛ ፍርድ ቤት ማለት ነው ?

በክልከላ ላይ የሚቀርብ ይግባኝ [የወ.መ.ሥ.ሥ.ህ.ቁ. 75]

- በሃያ ቀን ውስጥ መቅረብ በአለበት

- ይግባኙ ከቀረበ በኋላ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል። ይግባኝ የለውም።

በዋስትና ጉዳይ ላይ የሚያነጋግሩ ነጥቦች

- 1. የዋስትና አቤቱታ ስለሚቀርብበት ቦታ

  - ከሥነ-ሥርዓት ህጉ አኳያ የከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች ጉዳዩ ሊቀርብላቸው ይችላል?
  - በፌደራል ጉዳዮች ላይ የክልሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አቤቱታው ሊቀርብለት ይችላል?
  - ህጉ አሃዳዊ ሥርዓት ውስጥ የነበረ መሆኑ እና አሁን ደግሞ በፌደራል ሥርዓት ውስጥ መገኘታችን ሁኔታውን ይለውጠዋል?

2. የጊዜ ቀጠሮ መዝገብ በተከፈተበት ሁኔታ ስለሚቀርብ የዋስትና ጥያቄ

- በጊዜ ቀጠሮ መዝገብ ላይ አቤቱታ ያቀረበ ሰው በሌላ መዝገብ የዋስትና አቤቱታ ሊያቀርብ ይችላል?
- ሁለቱም ጥያቄዎች በአንንዱ ፍርድ ቤት በቀረቡ ጊዜ ተቃርኖ አይኖርም? የጊዜ ቀጠሮው መዝገብ የተከፈተበትን ዓላማ አያስትም?

3. ዋስትናን ስለሚያስከለክሉ ጉዳዮች

- **RTD** የዋስትናን መብትን ሊያስከለክል ይችላል? በምን ሁኔታ ?
- የወ.ሀ.ቁ. 534(3)
  - ሁለት ሰው መሞት/ግልጽ ደንብ መተላለፍ/የሚያፈዙ ነገሮችን ወይም መጠጦችን መውሰድ እስከአሥራ አምስት ዓመት ያስቀጣል።
- የኒውክሊየር አረር ይዞ ተገኝ ቷል መባል ዋስትናን ሊያስከለክል ይችላል ?

4. በዋስትና መፍቀድ ላይ ስለሚቀርብ ይግባኝ

- ዋስትና በመፍቀድ በሚሰጥ ውሳኔ ላይ ይግባኝ መጠየቅ ይቻላል ?
- የህጉ ሃሳብ ምንድነው ?
- ይግባኝን ከመከልከል ጋር አያይዞ ብቻ ማንሳቱ ምን ማለት ነው?
  - የዋስትናን ይግባኝ ከሌሎች ይግባኞች ተለይቶ በዚህ ክፍል ላይ ለምን መጣ?
  - የይግባኝ ጊዜውስ ከሌሎች ለምን ተለየ?
  - በመጀመሪያ ደረጃ የሚሰጠው ውሳኔ በቂ ስለሆነ በተጠርጣሪዎች ላይ ሌላ ፍርሃት ማንገስ አይገባም፣ የህዝብ ጥቅም ዕምብዛም አይጎዳም በማለት
    - ዓቃቤ ህግ ዋስትናን ለማስከልከል ተደጋጋሚ ጥረት እንዳያደርግ ገደብ ለማድረግ ነው?

5. በጥፋተኝነት ወይም በነፃ በመሰናበት በተሰጠ ውሳኔ ላይ በሚቀርብ ይግባኝ ላይ የሚቀርብ የዋስትና አቤቱታ

- ሀ. በጥፋተኝነትና በቅጣት ላይ ይግባኝ ሲቀርብ [የወ.መ.ሥ.ሥ.ሀ.ቁ. 188]

  ቅጣቱ ሊገደብ ይችላል - በዋስ ይለቀቃል ማለት ነው።

- ስለዚህ በዋስ ለመልቀቅ ምን ሁኔታዎች ያስፈልጉናል?

- ለ. በነፃ የተሰናበተ ሰው በይግባኝ ክርክር ላይዋስትና እንዲያቀርብ

  መጠየቅ አለበት?

  ድርጊቱ ከመነሻው ዋስትና የሚያስከለክል መሆን አለመሆኑ ዋስትና

  ለማስከልከል ፋይዳ አለው? ለምን

What is discharge? Is grant of bail discharge?